## የTAND አመራር "መኮነን ዘለለዉ" እና ጓደኞቹ ያዘጋጀዉ የስየና የገብሩ አስራት የክብር እንግዳነት የቴሌ- ኮንፈረንስ ዉይይት ተቃዎሞ ገጥሞት ከ45 ደቂቃ ባልረዘመ ጊዜ ዉስጥ ተበተነ!

ከጌታቸዉ ረዳ - (ሳን ሆዘ ካሊፎርኒያ) -Monday, June 23, 2008

ድሮ የህወሓት ታጋይ በየነበረዉ "መኮነን ዘለለዉ" ፡ በአሁኑ ወቅት የTAND የአመራር አባል በሆነዉ ግለሰብ "ሰብሳቢነት" የተካሄደዉ ከ20 (ሃያ) የማይበልጡ የትግራይ ተወላጆች በሚስጢር ተዘጋጀተዉ "የቴሌ-ኮንፈረንስ" ዕሁድ በፈረንጆች አቆጣጠር በJune 22, 2008 ስየ አብራሃ፡ ገብሩ አስራት፤ አረጋዊ በርሄንና ምናልባትም በለምለም ስም የቀረበች (አረጋሽ አዳነች -ነች የሚሏት በጥርጣሬ) የክብር እንግዶች ሆነዉ ለማካሄድ በተጠሩበት ኮንፈረንስ ከ45 ደቂቃ በማይበልጥ ዉይይት በሗላ እነ ስየ አብራሃንና እነ ገብሩ አስራትን ለመቃወም በሚስጢር ወደ ኮንፈረንሱ በገቡት ኢትዮጵያዊ መንፈስ ባነገቡ ግለሰቦች ጠንካራ ተቃዉሞ ገጥሞት ተሰብሳቢዎቹ ወደ ግል አስነዋሪና ብልግና ወደ ተሞላበት የእርስ በርስ ተራ ስድብ ዉስጥ በመግባታቸዉ እንዲወያዩባቸዉ ለዉይይት የቀረቡት 4 አጀንዳዎች ሳይደመጡ ኮንፈረንሱ ተቋርጦ እንዲዘጋ ተገዷል።

የኮንፈረንሱ አዘጋጆች እንዲወያዩባቸዉ ያቀረቡዋቸዉ 4 አጀንዳዎች ባጭሩ የሚከተሉት ናቸዉ።

1-የትግሉ ዉጤት። ይላል፤ ስለ (ኤርትራዊዉ ወያነ ትግራይ TPLF) ማለቱ ነዉ።

2- የህዝቡስ ትግል በምን መልኩ ይቀጥል?

3-በትግሉ ዉስጥ፤ የናንተስ ተራ ምን መሆን አለበት

4-ከኢትዮጵያ ታጋዮች ጋርስ በምን መልኩ ብንተባበር ይሻላል?
የሚሉ ናቸዉ።

ከተሰብሳቢዎቹ መሃል ቀደምት የኢድዩ እና ኢሕአፓ ታጋዮች እንኳ ቢኖርባቸዉም፤ ከአንድ የኢዲዩ ታጋይ በስተቀር እነሱም በአንጃዉ በነስየ አብራሃና በነገብሩ አሰራት አፍቃሬነት ዉስጥ ስለተሰባሰቡ፤ የትግራይ "ሕዝብ" ትግል እያሉ የሚጠሩት አጀንዳ ያኮላሹትንና ብዙ ብሔራዊ ወንጀሎችንና የሕዝብ ድምጽ በጠመንጃ ስያፍኑ የነበሩ እነ ስየና እነ ገብሩን መቃወም ቀርቶ የተቃወሙትን ሁሉ በተራ ስድብ ለማስቆም ሞክረዋል።

የኮንፈረንሱ የክብር እንግዶች ተብለዉ፤ (በመኮነን ዘለለዉ አጠራር "ዓበይቲ ሰባት" (ታላላቅ ሰዎች) ዛሬ ሥልጣን ዉስጥ የሌሉ ሦስቱም የወያኔ አመራሮች በተገለጹት አጀንዳዎች ላይ "ነካ- ነካ" እያደረጉ አስተያየታቸዉን ከሰጡ በሗላ፤ በአንድ የኢድዩ ነባር ታጋይ የነበረ ተቃዎሞ ደረሳቸዉ። "ወንድሞቻችን ጥርግርግ አድርጋችሁ በየምክንያቱ ፈጃችሗቸዉ!"፤ "ሕዝባችን የምትሉትን ሕዝብ ባፍ ጢሙ" ደፋችሁት!' 'አገራችን ሸጣችሗት!' 'ለኢትዮጵያ ባንዴራ ክብር የማትሰጡ ወራዶች!'፡ 'ነብስ በሎች!' 'ወደባችን ዘጋችሁት!' 'ምኒሊክ ኤርትራን ለጣልያን ሸጠ፤ እያላችሁ ስትዋሹን፡ ዛሬ ኤርትራን ማን አንደሸጠ አስመሰከራችሁ! ትግራይ ሕዝብ በናንተ ተዋርዷል! እኛ የትግራይ ሰዎች ታሪክና አገር "ሻጭ፤ ቸርቻሪ" እየተባልን በናንተ ታሪካችንንና ክብራችን ተዋርዷል!" አሁን እናንተ ስለ ዲሞክራሲ አዚህ የምትዘላብዱት ሰዉ ያምነናል ብላችሁ ነዉ?!" ከቶ እናተ ምን በደላችሁ! ይህ ሁሉ ክብር ለአገር ሻጮች እየሰጡ የሚያዋርዱን እነኚህ እዚህ እናንተን የጋበዙ የታሪክ "እባሶች-ጥራጊዎች" (አብረዉ ከናንተ ጋር ድሮ በትግሉ ወቅት ህዝብ ሲበድሉ የነበሩ)

ናቸዉ እንጂ እንናተማ ምን ታረጉ?!' እናንተ እዚህ ሳይሆን ስለ አገር "ክህደታችሁ" እስር ዉስጥ ነበር መግባት የሚገባችሁ!!!

በማለት አቶ ሽሻይ (አቶ ሽሻይ ዑቕባዝጊ) የተባለ ድሮ የኢድሕ ታጋይ የነበረ ኢትየጵያዉ ትግራይ ሰዉ እነኚህ "መደመጥ የለባቸዉም" "ድምጻቸዉ ልሰማ አልሻም፡ ሕዝብና አገር የሸጡ የበደሉ ናቸዉ፡ ኮንፈረንሱን ዝጉት! አሁኑኑ!" በማለት ከፍተኛ ተቃዎሞ (ፕሮቴስት) በማድረጉ፤ በመጨረሻ ለረጅም ጊዜ የስድብ እንካ ስላንትያ ፍጥጫዉ በመግባት ንትርኩ "ድሮ በወያኔና በኢድዩ ታጋዮች መሃል ወደ ነበርዉ ስድብና የመናናቅ ፍጥጫ 'ቴንሽን" ዉስጥ ስለተለወጠ ኮንፈረንሱ እንዲዘጋ ተገደደ።

"አቶ ሽሻይ ዑቕባዝጊ" ስየ አብራሃንና ገብሩ አስራትን ስለ የባሕር ወደባችን ማጣት ምክንያት እነሱ መሆናቸዉና ተጠያቂ መሆናቸዉንና እንደዙሁም አሁንም ኤርትራ የኢትዮጵያ ኮሎኒ ነበረች የሚለዉን እምነታቸዉ መተዋቸዉንና አለመተዋቸዉን፤ ከተዉትስ ባሕሩና ህዘቡ ከኛ ጋር ያስነጠቁን ጥቅማችንና ቤተሰባዊነታችን አንዱ አንዱን ሳይበድል 'ያበላሻችሁትን በምን መንገድ ይካስ ትላላችሁ?' ብሎ ከወጣራቸዉ በሗላ 'ከአመጓሾቻቸዉ አንዱ ፤ ግንፍል ብሎ "አቶ ሽሻይ ዑቕባዝጊ በተራ የአረብኛ ቋንቋ በስድብ ሲዘልፏቸዉ፤ አንዳንዶቹም "በዚህ ኮንፈረንስ አልተጋበዝክም "እረፍ" ስለ ኤርትራና ስለ ወደብ እንድንወያይ እዚህ አልመጣንም!" ሲለዉ፡- "አቶ ሽሻይ ዑቕባዝጊ" የወያኔ ጉድ ወደ መዘክዘኩ አልህ እና ስድብ ዉስጥ ሲገባ "እነ ስየ፡ እነ ለምለም (አረጋሽ አዳነ ነች "በለምለም' ስም ስትጮህ የነበረችዉ ይላሉ አንዳንድ ታዛቢዎች እንደገለጸዑት) እነ ገብሩ አስራት" "እንደነገጠች አይጥ ዉልቅ፡ዉልቅ" ብለዉ ከቴሌ ኮንፈረንሱ ተሰናበቱ።

በምስጢር በጓደኝነትና በዘመድ አዝማድ በጎጥ ስብስብ እየተጠራሩ እነ ስየና እና እነ ዝብሩ ኢትየጵያን ወደ ዲሞክራሲና ወደ ነጻነት ይመሯታል ብለዉ ለነኚህ ክብር ሰጥተዉ አሁንም በበሰበሰዉ ጎዳና ለመጓዝ የሚጥሩ ሰዎች አገሪቷን እንደገና ወደ ሌላ ጠማማና እልክ ሽኩቻ ዉስጥ ወደሚያስገባ ሁኔታ እየፈጠሩ መሆናቸዉን ካሁኑኑ ቢገነዘቡት መልካም ነዉ እንላለን። ከዚህ ዉስጥ ለዉስጥ (ስለ እኛ ስለ ትግራይ ሕዙብ) ባምቻና በጋብቻ፤ በጓደኝነት እየተጠራሩ ተንኮል የተሞላበት ስብስብ የሚያደረጉ ኮንፈረንሶች ከቀጠሉ፤ የስብሳቢዎቹ ማንነትና፤ "ጉድ" ይፋ በማዉጣት ማንነታቸዉን ለማጋለጥ የምንገደድ መሆናችነን ካሁኑኑ ለመግለጽ እንወዳልን። በሕዝብ ስም እየተሰበሰቡ፤ ከ እነ ስየና ከ እነ ገብሩ፤ ከእነ መለስና ወዘተ... እየተሞዳሞዱ ኮንፈረንስ ሲያካሂዱ ሌሎች ዜጎችም 'እኛም የ ህዝቡ አካል ነንና ሃሳባችን እንስጥ በሚሉት ላይ ተረባርበዉ በቡድን የሚሸርቡና ዲሞክራሲአዊ የንግግርና የፕሮቴስት (የመቃወም)፤ የመጮሕ፤ የመሰልፍ፤ ስብሰባዉ እንዳይካሄድ የማወክ ... ተናጋሪዉ እንዳይደመጥ የማወክ መብቶችን የሚዘጉ ሁሉ፤ ማወቅ ያለበቸዉ፤ ሰዎችን በትእግስት መጠበቅና ማቀዝቀዝ አንጂ "እኛ ብዙ ነን እሱ አንድ ነዉ፤ ተረባርበን አፉን እናስይዘዉ" የሚለዉ ከቶዉንም ለጊዘዉ እንጂ ዘላቂነት አይኖረዉም። እነ ስየንና እነ ገብሩን እንዲመሯችሁ የምታላዝኑ ሁሉ ተቃዋሚዉን "አቶ ሽሻይ ዑቕባዝጊ ገበሬ፤ ገሪባ፤ የገበሬ ልጅ.. የአጎቴ የፊታዉራሪ እገሌ በቅሎ ያዥ የነበርክ ... " የሚሉትን ስድቦች በመሳደባችሁ ስልጡን ምሁራኖች መሆናችሁ ለማሳት ገበሬዉንና የገበሬ ልጅ ማንኳሰሳችሁ ለትዝብት ይጥላችሗል። ገበሬዉን የምትንቁ "ከተሜዎችና አራዳዎች" "ምሕረቱን ይስጣችሁ!" እነ ገብሩ እንዲመሯችሁ ጊዜ ከምታጠፉ በሳዉዲ አረብ እና በግብጽ ምድር ዉስጥ ታስረዉ በሃይማኖታቸዉ ብቻ ተወንጅለዉ 5000 ጅራፍ በቀን 50 ጅራፍ እንዲገረፉና 10 ዓመት ተፈርዶባቸዉ፤ የሚሰቃዩትን 30 የትግራይ ተወላጆች ተሰባስበን እንርዳ፤ ሰላማዊ ሰልፍ እንዉጣ፤ ተቃዎሞ እንጻፍ። ብየ በዌብ ሳይቴ ስለምናችሁ አንዳችሁም እንኳ ለዚህ ቅዱስ ጥሪ አልመለሳችሁልኝም። ወያኔ የናቃቸዉ፤ ጊዜ የጣላቸዉ፤ የትግራይ ስደተኞችን ቴሌ ኮንፈረንስ ጠርቶ ከመርዳት ይልቅ፤ ሕዝብን የበደሉ ወያኔዎች አንዲመሯችሁ ለድሆቹ ጊዜ አጥታችሁ በዘመድ አዝማድ በጓደኛነት

በምስጢር እየተሰባሰባችሁ በቴሌ- ኮንፈረንስ ለወያኔዎች መማጸናችሁ ሌላዉ አሳዘኙ ገጽታዉ ነው:: "አሁንም ትግሉ በሁሉም ዘርፍ ይቀጥላል"

ጌታቸዉ ረዳ
2000 ዓ/ም

**የእርማት ማስታዎሻ!**

በእነ መኮንን ዘለለዉ የተዘጋጀዉ እነ ስየ አብርሃና ገብሩ አስራትን ያስተናገደ በምስጢር ሊካሄድ የታሰበዉ ቴሌ ኮንፈረንስ ባለፈዉ ቅጂ *በአገር ወዳዱ ኢትዮጵያዊ አቶ "ሸሻይ ዛና" የተባለዉ በስሕተት ስለሆነ "አቶ ሸሻይ ዑቕባዝጊ (በትግራይ ዉስጥ በሽሬ አወራጃ የአድያቦ ተወላጅ) ተብሎ ይነበብ:: "አቶ ሸሻይ ዑቕባዝጊ" የነ "መብራህቱ አርዓዶም" ወዳጅ ናቸዉ:: ሸሻይ ዛና እና ሸሻይ ዑቕባዝጊ የተላያዩ ግለሰቦች ናቸዉ:: ስሕተቱ የኔ የጸሃፊዉ ስለሆነ ይቅርታ::*

**ጌታቸዉ ረዳ!**